አንደኛ ዓመት ቁጥር 2
1st Year No. 2

ባሕር ዳር ግንቦት 16 ቀን 1985
Bahir Dar 24th May 1993

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
የክልል 3 መስተዳድር

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE GOVERNMENT OF REG. 3
IN THE TRANSITIONAL GOVT. OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በክልል 3 መስተዳድር ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ. ሣ. ቁ. 312 P. O. BOX 312

ግ ው ጫ

በቀጽ ቁጥር 2/1985 ዓ/ም
የክል ሦስት የሽግግር
መስተዳድር ሕገ-መንግሥት ገጽ 17

CONTENT

PROCLAMATION No. 2/1993
CONSTITUTION OF THE TRANSITIONAL
GOVERNMENT OF REGION THREE Page 17

መ ቅ ድ ም ፡

ብዬር /ብዬረሰቦች/ የእኩልነት መብት ተነፍገው ፡ የአገሪቱ አብዛኛው ሕዝብ በብዬራዊ ጭቆና ሥር ወድቆ ሲማቅቅበት ፡ በዚህም ደግሞ የብዬሮች እስር ቤት በመ ባል ስትታወቅ የኖረችው ሀገራችን በታጋይ ልጆቿና ሕዝቦቿ ተጋድሎ ወደ አዲስ የድል ምዕራፍ በመግ ባት ላይ በመሆኗ ፡

አዲሱ የሰላምና የዴሞክራሲ ምዕራፍ ከሰኔ 24-28/83 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው ታሪካዊ የሰ ላምና የዴሞክራሲ ጉባኤ የተበሰረና ጉባኤው ባፀደቀው ቻርተርም የተረጋገጠ በመሆኑ ፡

Introduction:

Whereas our country, where nations/nationalities have been denied equality and where the majority of the people has been suffering under national oppression, and for this used to be known as the prison of nations is now embarking upon a new chapter of victory by the struggle of her combatant children and peoples;

Whereas the new chapter of peace and democracy is heralded by the historic conference of peace and democracy held in Addis Ababa from July 1 to 5, 1991 and is ensured by the Charter which the conference has approved;

ሕምሴ 15/ 83ዓ/ም በኒጋሬት ጋዜጣ ታትሞ በወጣው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ለረዥም ዘመናት ታፍኖ የኖረው የሕዝቦችና የግለሰቦች መብትና ነጻነት የተከበረ ፣ የብሄሮችና የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ገደብ በማይደረግበት መረጋገጡ የታ ወጀ በመሆኑ ፣

በክልላችን የሚገኙ ብሄር /ብሄረሰቦች/ እንደማንኛ ውም ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ በቻርተሩ ተጠቃሚዎች ስለ ሆኑ ፣ በተለይም ደግሞ በስሙ ሲነገድበት ፣ የሌሎች ጭቁን ወገኖችን መብትና ጥቅም ለመርገጥ ገዥ መደ ቦች እንደመሣሪያ ሊጠቀሙበት ፣ በኢትዮጵያ አንድነ ትም ስም ለእልቂትና ለድሕነት ሲዳረግ የኖረው ጭቁን የአማራ ብሄርና ሌሎችም ሕዝቦች በተቀየሰው እኩል ነት ተጠቃሚ በመሆናቸው ፣

የክልላችን ሕዝብ በቻርተሩ ተጠቃሚነቱን ከረጋገጠ በኋው ከንዋኔዎች ውስጥ በራሱ ብሔራዊ ክልል የሽግ ግር መስተዳድር የመመስረትና ራሱን በራሱ ለማስተዳ ደር መብቃቱ አንዱ አቢይ ድል በመሆኑ ፣

ይህል ደረጃ የተመሰረተው ብሄራዊ ክልላዊ የሽ ግግር መንግሥት ክልሉን የሚያስተዳድርበት ፣ የሚነበ በትና የሚመራበት ሕገ- መንግሥት ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮችን ስለማቋቋም የተወ ከኮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/1984 አን ቀጽ 9/1 የክልል ምክር ቤቶች የራሣቸውን ሕገ- መንግ ሥት የማውጣት ስልጣን በተሰጣቸው መሰረት የሚከተ ለው የክልሉ የሽግግር ወቅት ሕገ-መንግሥት ታውጇል ።

ክፍል 1 ፤

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ፤

አንቀጽ 1. አጭር ርእስ ፤

ይህ አዋጅ የክልል ሶስት የሽግግር መስተዳድር ሕገ -መንግሥት አዋጅ ቁጥር 2/85 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

Whereas the right and freedom of peoples and individuals that had for long been suppressed are respected and the guaranteeing of the rights of nations and nationalities to self-determination are unrestrictedly proclaimed by the Transitional Charter of Ethiopia in the Negarit Gazeta issued on July 22, 1991;

Whereas the nations/nationalities living in our region will surely benefit from the Charter as any of the oppressed peoples; and whereas the other peoples and particularly the Amhara nation, in whose name they have been profiting, whom the ruling classes have made instrumental to suppress the rights and interests of other peoples, and whom they have made a victim of massacre and deprivation in the name of Ethiopian unity, have been beneficiaries from the outlined equality;

Whereas among the activities which have proved that the people of our region is beneficiary of the Charter, being able to establish a transitional government in its own regional territory and to administer itself is one great victory;

Whereas it is found to be essential to issue a constitution by which the national regional transitional government shall administer, build up and give leadership to the region;

Now, therefore, in accordance with article 9/1 of the proclamation No. 7/1992 that was issued by the Council of Representatives for establishing national regional governments which gives the authority to regional councils to promulgate their own constitutions, the following Transitional Constitution of the Region is hereby proclaimed.

PART 1
General Provisions

Article 1. Short Title

This proclamation may be cited as the constitution of the Transitional Government of Region Three, proclamation No. 2/1993.

አንቀጽ 2. ትርጓሜ ፣

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የሽግግር ሕገ-መንግሥት አዋጅ ውስጥ ፣

2.1. « ማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት » ማለት የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ማለት ነው ።

2.2. « ቻርተር » ማለት ሐምሌ 15 ቀን 1983 ዓ/ም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ 50ኛ አመት ቁ. 1 የታወጀው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ነው ።

2.3. «ሕገ-መንግሥት » ማለት የክልል 3 የሽግግር መስተዳድር ሕገ-መንግሥት ነው ።

2.4. «የክልል 3 ሕዝብ» ማለት የአማራ ፣ የአገው ካሚረኛ ፣ የአገው አውንጊኛ ፣ የአርሞን ብሄርና በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ብሄር/ብሄረ ሰቦችን/ ያካተተ ነው ።

2.5. « የክልል ሦስት መስተዳድር » ማለት በሰሜን የትግራይ ክልል ፣ በምስራቅ የክልል ሁለት ፣ በደቡብ ክልል አራት ፣ በምእራብ ክልል ስድስትና ሱዳን የሚያዋስኑት ሆኖ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የቆመ የሽግግር ወቅት መስተዳድር ነው ።

ክፍል 2 ፣

ምዕራፍ አንድ ፣

የሕዝቦችና የብሄር/ ብሄረሰቦች/መብቶች ፣

አንቀጽ 3

የክልል ሶስት ሕዝብ በማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ቻርተር መሰረት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት አለው ። በዚህም መሰረት ፣

1. የራሱን ማንነት የመጠበቅና የማከበር ፣ ባሕሉን ፣ ቅርሱንና ታሪኩን የማበልጸግ እንዲሁም

Article 2. Definition

In this Transitional Constitution, unless the context otherwise requires,

2.1 " Central Transitional Government " shall mean the Transitional Government of Ethiopia.
2.2 " Charter " shall mean the Transitional Charter of Ethiopia promulgated in the 50 th year, No. 1, Negarit Gazeta, issued in July 22, 1991.
2.3 " Constitution " shall mean the Constitution of the Transitional Government of Region Three.
2.4 " The people of Region Three " shall mean the composition of the nations / nationalities of Amhara, Agaw Khamir, Agaw Awngi, Oromo and others inhabiting the region.
2.5 " The Government of Region Three " shall mean a transitional government established for self - administration in the area bounded by the Region of Tigray in the north, by Region Two in the east, by Region Four in the south, and by the Region Six and the Sudan in the west.

PART 2

Chapter One

The Rights of Peoples and Nations /Nationalities

Article 3.

According to the Charter of the Central Transitional Government the people of Region Three has the right to self-determination. Accordingly:

1. The people has the right to respect and preserve its identity, to enrich its culture, heritage, and

በቋንቋው የመጠቀምና ቋንቋውን የማሳደግ መብት አለው ።

2. በራሱ መልክአ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመጨረስና ራሱን በራሱ የማስተዳደር እንዲሁም በማዕከላዊው መንግሥት ፣ በነጻነት፣ እድሉ በሌለበትና ተገቢ በሆነ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሣትፎ የማድረግ መብት አለው ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ ፣ ተረገጡ ፣ ወይም ተሸረሸሩ ብሎ ባመነበት በአንድነት ውስጥ ሆኖ ሊያስተገብራቸው ባልቻሉበት ጊዜ የራሱን እድል በራሱ እስከ ነጻነት ድረስ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል ።

አንቀጽ 4.

በለዋጅ ቁ. 7/1984 አንቀጽ 9 እና 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ሶስት የሽግግር መስተዳድር የውስጥ ጉዳዮችላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት የክልሉ ምክር ቤት ነው ።

ክፍል 3፡

- የግለሰብ መብቶች ፡

አንቀጽ 5.

ማንኛውም ግለሰብ በብሄር (ብሄረሰብ) ፣ በጸታ ፣ በሃይማኖት ፣ በዘር ፣ በሥራ ዓይነት ፣ በማኅበራዊና በሌላም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግበት በሕግ ፊት እኩል ነው ።

አንቀጽ 6

ማንኛውም ግለሰብ የንግግር፣ የጽሑፍ፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ትእይንተ-ሕዝብ የማድረግና በፓርቲ እስከ መደራጀት ነጻነቱ የተረጋገጠ ነው ።

አንቀጽ 7.

1. የማንኛውም ግለሰብ የሕሊና ፣ የሃይማኖትና የእምነት ነጻነት የተረጋገጠ ነው ።

history, as well as to use and develop its language.

2. The people has the right to determine its own affairs and to administer itself within its geographical territory as well as to make a free and effective participation with a fair and proper representation in the Central Government.

3. Where the people convinces itself that the rights provided under this article, sub-articles one and two were restricted, violated, or fragmented and where it finds that it could not enforce its rights within unity, it may implement its right to self-determination up to secession.

Article 4.

Without prejudice to the provisions under article 9 and 10 of proclamation No. 7/1992, the Regional Council is the highest political authority in the internal affairs of the Transitional Government of Region Three.

PART 3

Individual Rights

Article 5.

Every person is equal before the law irrespective of his /her nation / nationality, sex, religion, tribe, occupation, social status or any other condition.

Article 6.

The right of every person to the freedom of speech, writing, meeting, demonstrating, and organizing up to a political party is guaranteed.

Article 7.

1. The freedom for every person of conscience, religion and belief is guaranteed.

2. የክልሉ የሽግግር መስተዳድር በሃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ አይገባም ።

አንቀጽ 8.

1. የግንኛውም ግለሰብ ሰብአና አለመደፈር የተረጋገጠ ነው ።

2. የግንኛውም ግለሰብ መኖሪያ ቤት አለመደፈር የተረጋገጠ ነው ። ሕግ በግልጽ ከሚደነግገው በስተቀር ማንም ሰው ያለባለቤቱ ፈቃድ ከሌላ ሰው መኖሪያ ቤት መግባትም ሆነ ንብረትን ወይም መል እክቱን ሊፈትሽ አይችልም ።

አንቀጽ 9.

1. ሕግ በግልጽ ከሚደነግገው በስተቀር ማንም ሰው እጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈጽም ካልተገኘ አይያዝም ።

2 ማንኛውም የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ወደ ፍ/ቤት መቅረብ አለበት ። ሆኖም ይህ ጊዜ ወደ አቅራቢያው ፍርድ ቤት ለመድረስ የሚያስፈል ገውን ጊዜ አይጨምርም ።

3. ማንኛውም ሰው ከለ ፍርድ ቤት ውሣኔ ወይ ንም ትዕዛዝ በማንኛውም ሌላ ባለሥልጣን የተያዘ ወይም የታሰረ ወይም እንዳይንቀሣቀስ የተከለከለ እንደሆነ ይህ አድራጉቱ እንዲወገድለት ራሱ ፍ/ቤት ቀርቦ የማመልከት መብቱ የተጠበቀ ነው ።

4. አድራጉቱ የተፈጸመበት ሰው በማናቸውም ምክንያት ራሱ ፍ/ቤት መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ማመልከቻውን ሌላ ሰው ሊያቀርብለት ይችላል ።

አንቀጽ 10.

ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ ካልሆነ ወይም ሕግ ከሚደነግገው በስተቀር ሕጋዊ ምስክርነት የመ ስጠት ግዴታ አለበት ። ሆኖም በኃይል ወይም በተ ጽእኖ እንዲመሰክር አይገደድም ። በኃይል ወይም በተጽእኖ የተገደደ የምስክርነት ቃል ሕጋዊነት አይ ኖረውም ።

አንቀጽ 11.

1. ማንኛውም ወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍርድ

2. The Transitional Government of the Region shall not interfere in religious matters.

Article 8.

1. The inviolability of every person is guaranteed.

2. The inviolability of every person's home is guaranteed. No one may enter the home of or search the property or the correspondence of another person without his/her permit except where the law clearly so prescribes.

Article 9

1. No person shall be seized except in flagrante delicto or as may be prescribed by law.

2. Any person seized shall be produced in court within 48 hours. However, this period shall not include the time required to reach the nearest court.

3. If any person is seized, detained, or in any way restricted his/her right of movement by any authority other than by the order of the court, he/she may bring the case before the court of law so that the action will be revoked.

4. If the victim himself/herself could not appear before the court for whatever reason, any other person could do so on his/her behalf.

Article 10

Every one has the duty to give legal testimony except against himself/herself or as may be prescribed by law. However, no violence or pressure may be applied to compel a person to testify. Any testimony obtained by violence or pressure shall be null and void.

Article 11

1. Any person criminally accused shall not be considered criminal

ቤት ክልተወሰነበት በስተቀር ጥፋተኛ ሆኖ አይቆጠርም ።

2. ማንኛውም ተከሳሽ እራሱ የመከራከር ወይንም የሕግ ጠበቃ የማቆም መብት አለው ። በከባድ ወንጀል ተከሶ የሕግ ጠበቃ ለማቆም አለመቻሉ ለተረጋገጠለት ሰው በሕግ በሚወሰነው መሰረት መንግሥት በነጻ ያቆምለታል ።

unless it is so determined by a court.

2. Every accused person has the right to defend himself or to appoint a defence counsel. To a person who is charged with a serious offence and his/her inability to appoint a defence counsel is proved the government shall appoint one free of charge as determined by law.

አንቀጽ 12.

ተከሳሽን የሚረዳ ካልሆነ በስተቀር የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሠራም ። ማለትም ተከሳሹ በተከሰሰበት ቦታና ወቅት ሲሰራበት የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንዲታይለት ሕጉን ጠቅሶ መከራከር ይችላል ።

Article 12

Except where it benefits the accused, criminal law may not apply retroactively. This means that the accused may invoke the penal code provisions effective at the place where and at the time when he/she is accused and may demand to be judged accordingly.

አንቀጽ 13.

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በክልሉ የመኖር ፣ የመስራትና የመዘዋወር ነፃነትና መብቱ የተጠበቀ ነው ።

Article 13

The freedom and right of all Ethiopians to live, work, and move in the Region is guaranteed.

አንቀጽ 14.

ማንኛውም ግለሰብ የመምረጥ የመመረጥ መብቱ የተረጋገጠ ነው ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ።

Article 14

The right of every person to elect and to be elected is guaranteed. The details shall be prescribed by law.

አንቀጽ 15.

1. ጋብቻ የሕብረተሰብ መሠረት በመሆኑ ተገቢ ጥበቃ ይደረግለታል ።

2. ልጆች ከጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ ሲወለዱ በሕግ ፊት እኩል ናቸው ።

Article 15

1. As marriage is the foundation of society, it shall be given due protection.

2. Children, whether born in or out of wed-lock are equal before the law.

አንቀጽ 16.

በቤተሰብም ሆነ በሕብረተሰብ ውስጥ የፆታ እኩልነት የተረጋገጠ ነው ።

Article 16

Equality of the sexes in family and in society is guaranteed.

አንቀጽ 17.

ማንኛውም ሰው ከይዞታው ባመረተውና ባፈራው ሀብቱ የመጠቀም መብቱ የተጠበቀ ነው ።

Article 17

Everyone's right to make use of his/her property produced from what is at his/her disposal is guaranteed.

አቀንጽ 18.

1. የግል ሀብት በሕግ የተጠበቀ ነው ።

2. ሆኖም መስተዳድሩ ለሕዝቡ ጥቅም አስፈ ላጊ ሆኖ ሲያገኘው የግል ሀብትን ወይም የግል ንብ ረትን ተገቢውን ክፍያ በማድረግ ሊገለገልበት ወይም ከሣ በመክፈል ግልጋሎት ላይ እንዲውል ማድረግ ይችላል ።

አንቀጽ 19

የግለሰብ መብቶች አጠቃቀምና ፣ የግዴታዎች አከ ባበር በሕግ ይወሰናል ። የግለሰብ መብቶች አጠቃ ቀም በሕግ ገደብ የሚደረግበት መንግሥትና የሕብ ረተሰብ ጥቅም እንዲሁም የሌሎች ግለሰቦች ነፃነቶ ችና መብቶች እንዲከበሩ ብቻ ነው ።

ክፍል 4 ፤

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር አወቃቀርና አሰራር ፤

ምዕራፍ ሁለት ፤

አንቀጽ 20.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር በ ክ ል ፣ በዞንና በወረዳ የሚዋቀር መስተዳድር ነው ። እንደ አስፈ ላጊነቱ ሌላም አመች አወቃቀር ሊኖረው ይችላል ።

አንቀጽ 21.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር የሕግ አውጭ ፣ የሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካላት ያሉት በክልሉ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው ።

ምዕራፍ ሦስት ፤

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር ምክር ቤት ፤

አንቀጽ 22.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር ምክር ቤት የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አውጭ አካል ነው ።

Article 18

1. Private property is protected by law.

2. However, if the government finds that public interest so requires, it can make use of private property with appropriate payment or compensation.

Article 19

The exercise of individual rights and the discharge of duties shall be determined by law. The exercise of individual rights may be limited by law only to protect the interests of the government and society as well as for the freedom and rights of individuals to be respected.

PART 4

The structure and Functions of the Regional Transitional Government

Chapter Two

Article 20

The Regional Transitional Government is a government to be structured at regional, zonal, and wereda levels. It may also include other useful units in the structure as is necessary.

Article 21

The Regional Transitional Government is the supreme power of the Region containing a legislative, an executive, and a judicial organ.

Chapter Three

The Council of the Regional Transitional Government

Article 22

The Council of the Regional Transitional Government is the highest law-making body of the Region.

አንቀጽ 23.

የክልሉ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብና ለማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ነው ።

Article 23

The Regional Council is accountable to the people which elected it as well as to the Council of Representatives of the Central Transitional Government.

አንቀጽ 24.

የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን የማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነው ።

Article 24

The term of office of the Regional Council is the same as that of the Council of Representatives of the Central Transitional Government.

አንቀጽ 25.

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሕዝብ በቀጥታና በምስጢር ይመረጣሉ ።

2. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ከእያንዳንዱ ወረዳ በሕዝብ ምርጫ ሦስት ተመራጮች ይሆናሉ ።

3. የተመረጠው ተወካይ ጥፋት ሲገኝበት በምክር ቤቱ የዲሲፕሊን ደንቦች መሠረት ምክር ቤቱ ከምክር ቤት አባልነት ሊያስወግደው ይችላል ።

4. አንድ የምክር ቤት አባል ሲሞት ወይም በሌላ ምክንያት ሲገለል በእሱ ምትክ ሌላ ተወካይ ይመረጣል ።

5. የሚተኩት የምክር ቤት አባላት አመራረጥ በሕግ ይወሰናል ።

Article 25

1. Members of the Regional Council shall be elected directly and secretly by the people.

2. Members of the Regional Council shall consist of three representatives from each wereda elected by the people.

3. When the elected representative is proved to have committed any disciplinary misconduct the Council may dismiss him/her from membership according to the disciplinary regulations of the Council.

4. When a member of the Council dies or is sacked for any reason, another representative shall be elected to substitute him/her.

5. The election procedure of the substitution of the Council members shall be determined by law.

አንቀጽ 26.

1. የክልሉ ምክር ቤት በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል ። ሆኖም የምክር ቤቱ ሊቀመንበር ወይም የምክር ቤቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት ከሦስት አንድ እጅ 1/3ኛ ስብሰባ እንዲደረግ ሲጠይቅ አስቸኳይ ስብሰባ ይደረጋል ።

2. ከምክር ቤቱ አባላት ጠቅላላ ቁጥር ሁለት ሶስተኛው ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምክር ቤቱ ምልአተ ጉባኤ ይኖረዋል ።

Article 26

1. The Regional Council shall hold a regular meeting once every three months. However, extraordinary sessions may be called by the chairman of the Council, or by the Executive Committee of the Council, or when one third of the members of the Council so request.

2. Two-third of the members of the Regional Council shall constitute a quorum.

3. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ማንኛውንም ውሣኔ ሊያሳልፍ የሚችለው ስብሰባ ከተገኙት የም ክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደገፉት ነው ። ድምጹ እኩል ከተከፈለ ጉዳዩ በሌላ ጊዜ እንዲታይ ማድረግ አለዚያም ጊዜ ሰጥቶ በመወያየት ለመሰባሰብ መቻል ይኖርበታል ።

3. Without prejudice to the provisions given in Article 50 of this constitution the Council can pass any decision when supported by a simple majority of the members of the Council present at the session. In case of tie -vote either the issue shall be adjourned or be discussed further, so that one side will persuade the other.

አንቀጽ 27.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት ሌሎች የመስተዳድሩ አካላት ሥልጣን ከሆኑ ጉዳዮች በስተቀር ሌላ በማንኛውም ጉዳይ ውሳኔ የማሳለፍ ስልጣን አለው ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግ ባር ይኖሩታል።

Article 27

Excepting the powers bestowed upon the other organs of the government by this constitution, the Council of the Regional Transitional Government is hereby empowered to decide on all other matters. Without prejudice to this, the Regional Council shall have the following powers and duties:

1. የክልሉን የሽግግር ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጐችን ያወጣል ፣ ያሻሽላል ፣ አፈጻጸማቸውንም ይቆ ጣጠራል

1. Enacts, amends, and ensures the observance of the transitional constitution and the other laws of the Region.

2. የክልላዊ መስተዳድሩን በጀት ያጸድቃል ።

2. Approves the annual budget of the Regional Government.

3.የክልሉን የአጭርና የረጅም ጊዜ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ እቅዶች ያጸድቃል ፣

3. Approves the long-term and short-term social and economic plans of the Region.

4. ማዕከላዊ መንግሥት ያወጣውን የገቢ ክፍፍል መነሻ በማድረግ የክልሉን የሽግግር መስተዳድር የገቢ ምንጮች ይወስናል ፣ ቀረጥና ግብር ይጥላል ፣ ከአገር ውስጥ የብድር ምንጮች ይበደራል ።

4. In accordance with the distribution of income fixed by the Central Government, determines the sources of revenue of the Regional Transitional Government, levies taxes and duties, and borrows from sources in the country.

5. በክልሉ የሚሰጡ ሕዝባዊ አገልግሎቶችን ይወስናል ። አስፈላጊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋ ሞችን ወይም ድርጅቶችን ያቋቁማል ።

5. Determines the public services to be rendered in the Region. Establishes the necessary social and economic institutions or organizations.

6. የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅ የሚያ ስፈልግ የጸጥታና የፖሊስ ኃይሎችን ያቋቁማል ።

6. Establishes police and security forces necessary to maintain the peace and security of the Region.

7 ክልሉ በአዋጅ ቁጥር 7/84 ለወረዳው ምክር ቤት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ ዞኖችን ፣ ወረዳዎችንና ከወረዳ በታች ያሉትን

7. Without prejudice to the power vested upon the Wereda Council by Proclamation No.7/92 the Region sets up the zones, the weredas, and units

ያዋቅራል ፤ የመሬት ስፋታቸውንና የሥልጣን ክልላቸውን ይወስናል ።

8. ከሌሎች ብሄራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮች ጋር በአዋጅ ቁጥር 7/1984 አንቀጽ 15 ንውስ ቁጥር 1 ላይ በተቀመጠው መሰረት የሚደረገውን ስምምነት ያጸድቃል ።

9. ከምክር ቤቱ አካላት መካከል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ፣ የምክር ቤቱን ሊቀመንበር ፣ ም/ሊቀመንበርና ጸሐፊ ይመርጣል ።

10. የክልሉ መስተዳድር የዳኝነት አካላትና የአቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትን ያቋቁማል ።

11. የኦዲትና የቁጥጥር አካል ያቋቁማል ፤ ዋና ኃላፊውን ይሾማል ።

12. የክልሉን ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ዳኞችን ለ7ቱ ዞኖች አንድ ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት እንዲሁም የሰባቱን ዞኖች ዳኞች ይሾማል ።

13. የክልሉን አቃቤ ሕግ መ/ቤት ዋና ጸሐፊ ይሾማል ።

14. የክልል መስተዳድሩን የልዩ ልዩ ቢሮ ኃላፊዎች ይሾማል ።

15. በማዕከላዊ መንግሥት ከሚወሰኑት በስተቀር የመስተዳድሩን አስፈጻሚ አካላትና ልዩ ልዩ ተቋማት ሥልጣንና ተግባር ይወስናል ።

16. የአካባቢውን ተፈጥሮ ለማልማትና ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ፣ መመሪያዎችንና ስልቶችን ያወጣል ።

17. በየሶስት ወር በሊቀመንበሩ አማካይነት ለማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ስለሥራው እንቅስቃሴ ዘገባ ያቀርባል ።

18. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚሽኖችን ያቋቁማል ።

that are below the wereda level; determines their boundaries and the territory of their authority.

8. Approves the agreements to be reached with other national regional governments in accordance with the article 15, sub-article 1 of the proclamation No. 7/92.

9. Elects members of the Executive Committee, the chairperson, the vice chairperson, and the secretary of the Council among the members of the same.

10. Establishes the judicial organs and the prosecutor's offices of the Regional Government.

11. Establishes regional auditing and control offices and appoints the heads.

12. Appoints the president and the judges of the Regional Supreme Court, a president, a vice president, and judges for each of the seven zones.

13. Appoints the secretary general of the offices of the prosecutor.

14. Appoints the heads of the various bureaus of the Regional Government.

15. Determines the powers and duties of the executive bodies and different institutions of the Regional Government excepting those that aro determined by the Central Government.

16. Produces systems, directives and methods that could enable to develop and preserve the Region's natural resources.

17. Submits, through the chairman, reports on its activities to the Council of Representatives of the Transitional Government every three months.

18. Establishes the necessary standing and ad-hoc commissions.

19. የራሱን የውስጥ ደንብ ያወጣል ።

ምዕራፍ አራት ፤

የክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፤

አንቀጽ 28.

የክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የክልሉ የሽግግር መስተዳድር ከፍተኛ ሕግ አስፈጻሚ አካል ነው ።

አንቀጽ 29.

የክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ሕጐችና ፖሊሲዎች አፈጻጸምን በሚመለከት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል ። እንዲሁም የክልሉን ሕጐችና ፖሊሲዎች በሚመለከት ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል ።

አንቀጽ 30.

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 27 ንውስ አንቀጽ 9 መሠረት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በድምፅ ይመረጣሉ ።

አንቀጽ 31.

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በጋራ ፣ በ ኮሚቴና በግል የመስተዳድሩን መ/ቤቶች ይመራሉ ።

አንቀጽ 32.

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ቀጥሎ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

1. በማዕከላዊ የሽግግር መንግሥትና በክልሉ ምክር ቤት የወጡ ፖሊሲዎች ፣ አዋጆች ፣ ደንቦች አቅዶች ፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል ።

2. የክልሉ የሽግግር መስተዳድር ልዩ ልዩ ተቋሞችን ፣ የዞን ፣ የወረዳ አስተዳደሮችንና ከዚያ በታች ያሉትንም በተግባር ይመራል ፣ ያስተባብራል ፣ ይቆጣጠራል ።

19. Adopts its internal regulations.

Chapter four

The Regional Executive Committee

Article 28

The Regional Executive Committee is the highest executive organ of the Regional Transitional Government.

Article 29

The Regional Executive Committee shall be accountable to the Council of Ministers as concerns the implementation of laws and policies of the Central Transitional Government and to the Regional Council as regards the implementation of Regional laws and policies.

Article 30

The members of the Regional Executive Committee shall be elected among the members of the Regional Council according to article 27 sub-article 9 of this constitution.

Article 31

Members of the Executive Committee shall lead the offices of the government jointly as a committee, and individually.

Article 32

The Executive Committee shall have the following power and duties.

1. Ensures the proper implementation of policies, proclamations, regulations, plans, directives and decisions enacted by the Central Transitional Government and the Regional Council.

2. Practically leads, coordinates, and supervises the various institutions of the Regional Transitional Government, the zonal, wereda and other administrative units.

3. የክልሉ የሽግግር መስተዳድርን የማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም የኢኮኖሚ ልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል ፣ለክልሉ ምክር ቤት ያቀር ባል ፣ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል ።

4. የክልል መስተዳድሩን በጀት ያዘጋጃል ፣ ለክ ልሉ ምክር ቤት ያቀርባል ፣ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል ።

5. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ ቅርሶችንና የተፈጥሮ ኃብቶችን ልማት ጥቅም ላይ ለማዋልና ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል ።

6. የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል ።

7. ከሌሎች የሽግግር መስተዳድሮች ጋር የማዕከ ላዊ የሽግግር መንግሥትና የክልሉን ምክር ቤት ሥልጣንና ኃላፊነት በማይጋፋ መልኩ በክልሉ ጉዳዮች ላይ ይደራደራል ፣ስምምነቶችን ይፈራረማል

8. የምክር ቤቱን አስቸኳይ ጉባዔ ይጠራል ።

9. በክልሉ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል

10. የክልሉን ሕዝብ ጥቅም ፣ደህንነትና መብት ለማስከበርና ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ።

11. ለክልሉ ምክር ቤትና ለማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ሥራው እንቅስቃሴ ዘገባ ያቀርባል ።

12. ምህረት ያደርጋል ፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰ ናል ።

13. በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግ ባራት ለማከናወን ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል ።

14. ከክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

3. Prepares and submits to the Regional Council plans and programs of social services and of economic development schemes of the Regional Transitional Government, and ensures their implementation when approved.

4. Prepares the annual budget of the Regional Government, submits it to the Regional Council, and when approved ensures its implementation.

5. Makes all the proper effort to utilize and preserve the international and national heritages and the development of natural resources that are found in the region.

6. Coordinates the standing and ad-hoc committees of the Council.

7. Without violating the power and duties of the Central Transitional Government and the Regional Council, negotiates on regional matters and signs agreements with other Transitional governments.

8. Calls extraordinary sessions of the Council.

9. Ensures the maintenance of law and order in the region.

10. Takes the necessary legal measures to protect and ensure the interest, security, and rights of the people of the region.

11. Submits reports on its activities to the Regional Council and to the Council of Ministers of the Central Transitional Government.

12. Grants amnesty; details shall be determined by law.

13. Enacts regulations and directives to exercise the powers and functions vested upon it in this article.

14. Performs other duties assigned to it by the Regional Council.

15. የዞን የአቃቤ ሕግ ፣ የኦዲትና ቁጥጥር ኃላፊዎችን ፣ የልዩ ልዩ መምሪያ ኃላፊዎችን ይሾማል ።

አንቀጽ 33.

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በወል ለሚወሰዱት እርምጃዎች የጋራ ፣ በተናጠል ለሚወሰዱት እርምጃዎች የግል ኃላፊነት አለባቸው ።

ምዕራፍ አምስት ፤

የክልሉ ምክር ቤት ሊ/መንበር፣ ም/ሊቀመንበርና ፀሐፊ፤

አንቀጽ 34.

1. የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር ፣ ም/ሊቀ መንበርና ፀሐፊ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 27/9 መሠረት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በድምፅ ይመረጣሉ ።

2. የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር ፣ ም/ሊቀ መንበርና ፀሐፊ የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል ።

አንቀጽ 35.

የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር ለክልሉ ምክር ቤት እንዲሁም በማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ ነው ።

አንቀጽ 36.

የሊቀመንበሩ ሥልጣንና ተግባር ፤

የክልሉ ምክር ቤት ሊ/መንበር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

1. የክልሉ የሽግግር መስተዳድር መሪ ነው ።

2. የክልሉ የሽግግር መስተዳድር አፈ-ጉባኤ በመሆኑ ከማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ጋር ይገናኛል ።

15. Appoints zonal prosecutors, heads of auditing and control, and heads of the various departments.

Article 33

Members of the Executive Committee shall be liable jointly for their joint activities, and individually for their individual activities.

Chapter Five

The Chairperson, vice chairperson, and secretary of the Regional council

Article 34

1.The chairperson, vice chairperson, and secretary of the Council shall be elected by vote from amongst the members of the Regional Council according to article 27/9 of this constitution.

2. The term of office of the chairperson, vice chairperson, and secretary of the Regional Council shall be the term of office of the Regional Council.

Article 35

The chairperson of the Regional Council shall be accountable to the Regional Council and to the Council of Ministers of the Central Transitional Government.

Article 36

The power and duties of the chairperson

The chairperson of the Regional Council shall have the following powers and duties:

1.Is the head of the Regional Transitional Government.

2. As is the spokesman of the Regional Transitional Government, communicates with the Central Transitional Government.

3. የክልሉን ምክር ቤት ስብሰባ ይጠራል፤ይመራል፤ ሥራውን ያስተባብራል ።

4. የክልሉን የሽግግር መስተዳድር ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ዳኞች፣የሰባቱን ዞኖች ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት እንዲሁም ዳኞችን ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያሾማል ።

5. የክልሉን የኦዲትና ቁጥጥር ፣ የአቃቤ ሕግና እንዲሁም የልዩ ልዩ ቢሮ ኃላፊዎችን በማቅረብ ያሾማል ።

6. የክልሉን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመራል፤ የልዩ ልዩ ተቋማት ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤ይቆጣጠራል ።

7. የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዓቱን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልላዊ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ።

8 የክልሉን የሽግግር መስተዳድር ሠራኮኞች ሹመት ፣ ሥልጣን ፣ አቀጣጠር ፣ አመዳደብ፣ ዝውውር ፣ ቁጥጥር ፣ዕድገትና ዲሲፕሊን በበላይነት ይመራል።

9. ቻርተሩ ፣ የግዕዝላዊ የሽግግር መንግሥት ሕጐችና ፖሊሲዎች እንዲሁም የክልል የሽግግር መስተዳድር ሕጐች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል ።

10. የክልሉ መስተዳድር አጠቃላይ እንቅስቃሴን የሚመለከት ሪፖርት በየጊዜው ለክልሉ ምክር ቤትና ለግዕዝላዊ የሽግግር መንግሥት ያቀርባል ።

11. በዚህ አንቀጽ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለማከናወን ደንጋጌ ያወጣል ።

12. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

3. Calls and chairs the sessions of the Regional Council and coordinates its duties.

4. Forwards for appointment to the Regional Council the president and the judges of the Supreme Court of the Regional Transitional Government, the president and the vice president of the seven zonal high courts and the judges.

5. Forwards for appointment the heads of auditing and control, the prosecutor's office, and the various bureaus.

6. Heads the Regional Executive Committee; coordinates and oversees the activities of the various institutions.

7. Heads the security and police forces established to ensure the security of the Region and to maintain law and order.

8.Heads the appointment, authority, employment, allocation, transference, supervision, promotion, and disciplinary activities regarding the workers of the Regional Transitional Government.

9. Ensures that the Charter, the legistlations, and policies of the Central Transitional Government as well as the laws, regulations and directives of the Regional Transitional Government are properly implemented.

10.Submits regular reports that deal with the general activities of the Regional Government to the Regional Council and the Central Transitional Government.

11. Issues rules to implement the powers and duties given in this article.

12. Performs other activities assigned to him/her by the Regional Council.

አንቀጽ 37.

የክልሉ ምክር ቤት ም/ሊቀመንበር ሥልጣንና ተግባር ፤

የክልል ምክር ቤቱ ም/ሊቀመንበር ፤

1. ሊቀመንበሩ ተግባሩን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል ።

2. በሊቀመንበሩና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል ።

አንቀጽ 38.

የክልል ምክር ቤት ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር፤

የክልል ምክር ቤቱ ፀሐፊ ፤

1. የምክር ቤቱን ጽ/ቤት ያደራጃል ፤

2. የምክር ቤቱን ሰነዶች ለአግባቡ ይይዛል ፤

3. የምክር ቤቱን ቃለ-ጉባኤ በሚገባ መያዙን ያረጋግጣል ፤

4. የጽሕፈት ሥራዎችን በኃላፊነት ይመራል

5. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

ምዕራፍ ስድስት ፤

አንቀጽ 39.

በክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የአንድ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትና የሌሎች የበታች ፍ/ቤቶች ብቻ ነው ።

አንቀጽ 40.

ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ ፤ ከሕግ በስተቀር በማንኛውም ሌላ ሥልጣን አይመሩም ።

Article 37

The power and duties of the vice chairperson of the Regional council.

The vice chairperson of the Regional Council:

1.Discharges the activities of the chairperson when the latter cannot perform his/her duties.

2. Performs duties assigned to him/her by the chairperson and the Executive Committee.

Article 38

The Power and duties of the Secretary of the Regional Council

The secretary of the Regional Council:

1.Organizes the office of the Regional Council:

2. Handles the documents of the Council property.

3. Ensures that the minutes of the Council-meetings are kept safe.

4. Manages all office works.

5. Performs other duties assigned to him/her by the Executive Committee.

Chapter Six

Article 39

Judicial power in the Region shall be vested only in one Regional Supreme Court and the other lower courts.

Article 40

Judges shall exercise their judicial function in complete independence; they shall be guided by no other authority except by the law.

አንቀጽ 41.

1. የዳኞች አመራረጥና አስተዳደር በሕግ ይወሰናል ።

2. የፍ/ቤቶች የዳኝነት የሥልጣን ክልል በሕግ ይወሰናል ።

አንቀጽ 42.

በሕግ ተለይተው በማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን ክልል ሥር ከሆኑት ጉዳዮች በስተቀር ከክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

አንቀጽ 43.

ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተግባራቸውን የሚያከናውኑበትን ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ የትርጉም አገልግሎት ይሰጣሉ ። ወይም አስተርጓሚ ይዞ መቅረብ ይችላል ።

አንቀጽ 44.

በዝግ ችሎት እንዲታይ በሕግ የተወሰኑ ምክንያቶች ካላጋጠሙ በስተቀር ማንኛውም ጉዳይ የሚታየው በግልጽ ችሎት ይሆናል ።

ክፍል አምስት ፤

ምዕራፍ ሰባት ፤

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ፤

አንቀጽ 45.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር የራሱ ሰንደቅ አላማ ይኖረዋል ። ዓይነቱና ትርጉሙ በሕግ ይወሰናል ።

አንቀጽ 46.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር አርማ በሕግ ይወሰናል ።

አንቀጽ 47.

የክልሉ የሽግግር መንግሥት ርዕሰ ከተማ ባሕር ዳር ነው ።

Article 41

1. The election and administration shall be determined by law.

2. The jurisdiction of courts shall be determined by law.

Article 42

Except the cases which are clearly vested in the jurisdiction of the Central Supreme Court, the decisions of the Regional Supreme Court shall be final.

Article 43

Where a party does not understand the language in which the court conducts the judicial proceedings, interpretation service shall be provided or the party may bring his/her interpreter.

Article 44

Except where in camera hearing may be justified for reasons specified by law, every case shall be heard in public.

PART 5

Chapter Seven

Miscellaneous Provisions

Article 45

The Regional Transitional Government shall have a flag of its own. The type and interpretation shall be determined by law.

Article 46

The emblem of the Regional Transitional Government shall be determined by law.

Article 47

The capital city of the Regional Transitional Government is Bahir Dar.

አንቀጽ 48.

የክልሉ የሽግግር መስተዳድር የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው ።

አንቀጽ 49

ይህ የክልሉ የመሸጋገሪያ ሕገ መንግሥት የሽግግር መስተዳድሩ የበላይ ሕግ ነው ፣ ማንኛውም የክልሉ ሕግና ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

አንቀጽ 50.

ሕገ መንግሥቱ ከክልሉ ምክር ቤት በስብሰባው ከተገኙት አባላት በሦስት አራተኛ 3/4ኛ እጅ በሚደገፍ ውሳኔ ብቻ ሊሻሻል ይችላል ።

አንቀጽ 51.

ይህ የክልል መስተዳድሩ ሕገ መንግሥት በዝክረ ሕግ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

ባሕር ዳር
ግንቦት 16 ቀን 1985 ዓ/ም

አዲሱ ለገሰ
የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር
ሊቀመንበር

Article 48

The working language of the Regional Transitional Government is Amharic.

Article 49

This Regional Transitional Constitution is the supreme law of the Regional Government; any law or decision contrary to this Constitution shall be null and void.

Article 50

The Constitution shall be amended only by a three-fourth (3/4th) majority decision of the members of the Regional Council in attendance during the session.

Article 51

This Constitution of the Regional Government shall be effective as of the date of its publication in the Regional Zikre Hig.

24 th, May ,1993
Bahir Dar
Addisu Legesse
Chairman of the Transitional
Government of Region Three